**በኮሎምቢያ ዲስትሪክት መንግሥት**
**የፓርክ እና የመዝናኛ መምሪያ**
**የትብብር እና የልማት ክፍል**

# የDPR የፕሮግራም ተባባሪ

**የፕሮግራም ተባባሪዎች በDPR የመዝናኛ ማዕከሎች ለተካፋዮች ያለምንም ክፍያ አዳዲስ ፕሮግራም የሚያቀርቡ ድርጅቶች ናቸው።**

የፕሮግራም ተባባሪ ለመሆን

የፕሮግራም ተባባሪ ለመሆን ፍላጎት ያለው አመልካች በDPR የማጣራት ሂደት ማለፍ ያስፈልገዋል። አንድ አመልካች ከዚህ በፊት ከዲሲ የሕዝብ ትምህርት ቤቶች (DCPS) ከትምህርት ውጭ አገልግሎት ሰጪ ለመሆን የፈቃድ ደብዳቤ ደርሶት ከሆነ፣ አመልካቹ ለDPR ማመልከቻ ከማስገባቱ በፊት የዚህን የፈቃድ ደብዳቤ ግልባጭ ለDPR ማቅረብ አለበት። በአንዳንድ ሁኔታዎች፣ የDCPS ፈቃድ አመልካቹን የDPR የፕሮግራም ተባባሪ እንዲሆን ተመራጭ አድርጎ ሊያቀርበው ይችላል። ሆኖም፣ DPR ለሕዝብ በቂ የሆነ ማስታወቂያ በማስተላለፍ በማንኛውም ጊዜ ምርጫውን ለማስፈጸም እና የማጣራት ሂደቱን ለመለወጥ መብቱ የተጠበቀ ነው።

አመልካቾች ከማመልከቻው እና/ወይም ከፈቃዱ ሂደት ጋር በተያያዘ ከDPR ገንዘብ ለመቀበል ብቁ አይደሉም።

ማመልከቻ ማቅረብ በፕሮግራም ተባባሪዎች ፕሮግራም ውስጥ ለመካፈል ዋስትና እንደማይሆን እባክዎን ያስታውሱ። ማመልከቻው ከተፈቀደ፣ አገልግሎት ሰጭው ህንጻው ውስጥ ከመግባቱ እና ፕሮግራሙን ከመጀመሩ በፊት ከDPR ጋር የስምምነት ውል መግባት ያስፈልገዋል።

ከDPR ጋር የፕሮግራም ትብብር ምሳሌዎች፣

| | | |
|---|---|---|
| ከትምህርት ውጭ ፕሮግራሞች | የአዛውንት ጤና እና ደህንነት | ወጣት ስፖርተኞች |
| STE(A)M ወርክሾፖች | የፈጠራ ኪነጥበቦች | የተለዩ ካምፖች |

የማመልከቻ ሂደት:

ደረጃ 1 - ድርጅቶቹ የፕሮግራሙን ዝርዝር ሃሳብ ለDPR ያቀርባሉ
ደረጃ 2 - የDPR ሠራተኛ ሀሳቡ ከተልዕኮው፣ ከራዕዩ እና ከግቦቹ ጋር መመጣጠኑን ይገመግማል። በተጨማሪም፣ የጊዜ/የቦታ መኖርን ጨምሮ
ደረጃ 3 - ሀሳቡ ተቀባይነት ካገኘ፣ ድርጅቱ ማመልከቻ ሞልቶ የድጋፍ መረጃዎችን ያቀርባል።
ደረጃ 4 - DPR ተስማሚነትን የማጣራት ሂደት ያካሂዳል
ደረጃ 5 - ማመልከቻው ከፀደቀ፣ DPR እና አመልካች የስምምነት ውል (MOA) ይገባሉ።

የፕሮግራም ተባባሪ የመሆን መስፈርቶች:

ከማመልከቻው በተጨማሪ፣ ድርጅቶች የኪሳራ የህይወት ዋስትና ሰርቲፊኬት፣ ለትርፍ የማይሠራ ድርጅት(የ501(c)(3) አቋም፣ (ነገር ግን በዚህ ብቻ ያልተወሰነ)፣ ከዕዳ ነጻ የመሆን ሰርቲፊኬት፣ ምስክሮች፣ በጀት እና የገንዘብ ዝርዝር፣ ወዘተ... ። በተጨማሪም፣ የስምምነት ውሉን ለማጠናቀቅ ከወጣቶች ጋር የሚሠሩ ሁሉም ሠራተኞችና የበጎ ፈቃድ ሠራተኞች፣ ከወንጀል ነፃ ማጣሪያን ማለፍ አለባቸው።

1. የኪሳራ የህይወት ዋስትና ሰርቲፊኬት

ሁሉም የፕሮግራም ተባባሪዎች የሚከተሉትን ዓይነቶች (ሆኖም፣ በዚህ ብቻ ያልተወሰነ) የህይወት ዋስትና ሰርቲፊኬት ማግኘት እና ይህንንም በDPR ህንጻ ፕሮግራም ከመጀመራቸው በፊት ለDPR መስጠት፣

(i) በኮሎምብያ ዲስትሪክት ህግ እና ቢያንስ $500.000 የቀጣሪ የኪሳራ መድን መሠረት ሙሉ ሽፋን የሚሰጥ የሠራተኞች ካስ መድን፤ ቢያንስ $1,000,000 የሰውነት ጉዳት ይሚሸፍን አጠቃላይ የንግድ የኪሳራ መድን "በደረሰበት ጊዜ"፣ የግል ጉዳት፣ የሞት እና የንብረት ጉዳት (የኮሎምብያ ዲስትሪክት መንግሥት፣ DC የፓር እና የመዝናኛ መምሪያ (DPR) እና አለቆቻቸውና ሠረተኞቻደው እንድ ተጨማሪ ተቆጥረው)፣ እና የአካል፣ የሞት እና ይንብረት ጉዳትን በአንድ ያጠቃለለ ከ$500.000 ያላነሰ የመኪና ካሳ መድን። ማንኛውም የተለያይየ ዓይነት እና ዋጋ የሚሸፍን አስቀድሞ በDPR መፈቀድ አለበት።

(ii) ቢያንስ $2,000,000 ተጨማሪ የዕዳ መድን (Umbrella liability insurance)

2. ቅድመ እና መጨረሻ ምዘናዎች

የፕሮግራማቸውን ስኬታማነት ለመገምገም የፕሮግራም ተባባሪዎች ለተሳታፊዎች የሚሰጠውን የቅድመ እና መጨረሻ ምዘናን ግልባጭ ለተሳታፊዎች መስጠት አለባቸው። የቅድመ ምዘና ጥናቱ የተሳታፊውን ከፕሮግራሙ መጀመሪያ በፊት የነበረውን ዕውቀትን እና/ወይም ችሎታዎችን መነሻ ያደርጋል። የመጨረሻ ምዘና ጥናቱ ተሳታፊው ከፕሮግራሙ ያገኘው ውጤት እውቀት እና/ወይም ችሎታዎች ላይ የሚያተኩር ነው።

3. የወንጀል ምርመራዎች

ከተፈቀደው የDPR ፕሮግራም ተባባሪዎች ጋር የሚሠሩ ሁሉም ሠራተኞች እና የበጎ ፈቃድ ሠራተኞች ፕሮግራሙ ከመጀመሩ በፊት የወንጀል ምርመራዎች ማድረግ አለባቸው። እባክዎን የሁሉንም ፕሮግራምዎን አስተናባሪዎች አድራሻ ለፕሮግራም ትብብር አስተዳዳሪው ይስጡ። ፕሮግራሙ ከትፈቀደ፣ እያንዳንዱ ሰው የበጎ ፈቃድ ሠራተኛ ማመልከቻ መሙላት አለበት። ማመልከቻው በ HYPERLINK "http://www.dnr.dc.gov/"www.dnr.dc.gov ይገኛል።

4. ተጨማሪ የሚጠየቁ መረጃዎች

ጥያቄዎች ካሉዎት ወይም ስለመጪው DPR ፕሮግራም ተባባሪ ተጨማሪ መረጃ ከፈለጉ፣ እባክዎን የDPRን የትብብር እና የልማት ቢሮን በ HYPERLINK "mailto:dpr.partnerships@dc.gov"dpr.partnerships@dc.gov ይጠይቁ